Athletics Integrity Unit

# ROAD TO PARIS

# ጉዞ ወደ ፓሪስ




aiu_athletics

aiu_athletics

aiu.athletics

community@athleticsinetgrity.org

www.athleticsintegrity.org

# ለ2024 የኦሊምፒክ ጨዋታዎች ለስፖርቱ ታማኝነት መመርያ

## ይህ በራሪ ወረቀት ለ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ጨዋታዎች ለሁሉም አትሌቶች እና የአትሌቶች ድጋፍ ሰጪዎች አስፈላጊ መረጃዎችን ያመጣል፡፡

For most accurate information cross reference with the English or French versions.

# በኦሊምፒክ ጨዋታዎች ጊዜ ድርጅታዊ ሀላፊነት

በፓሪስ ኦሊምፒክ ጨዋታዎች በአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ የሚሳተፉት ሁሉም አትሌቶች እና የአትሌት ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች በኦሊምፒክ ጨዋታዎች ወቅት በአለምአቀፍ ኦሊምፒክ ኮሚቴ አይ. ኦ. ሲ ህግ የተያዙ ናቸው።

በኦሊምፒክ ጨዋታ ጊዜ (እ.ኤ.አ ከጁላይ 18-ኦገስት 11ቀን 2024) የአለም አቀፍ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ህጎችን መጣስ በኦሊምፒክ ጨዋታዎች ላይ የሚያስከትለውን መዘዝ በተመለከተ በአለምአቀፍ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ቁጥጥር ይደረግበታል። ውጤቶቹም  ለምሳሌ ውጤቶቹ ውድቅ መደረግ፣ ሜዳሊያዎችን ማስወገድ እውቅና መንሳት ከጨዋታዉ ጊዜ በኋላ በሚተዳደረው በአትሌቲክስ ኢንተግሪቲ ዩኒት በሚመለከተው የአለም አትሌቲክስ ህጎች መሰረት ነው።

International Olympic Committee

ኢንተርናሽናል ኦሎምፕክ ኮምቴ -በኦሊምፒክ ጨዋታዎቹ ውስጥ በአትሌቲክስ ስፖርት ውስጥ ለሚካሄዱት የታማኝነት ፕሮግራሞች የአለማቀፍ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ዋና ሀላፊነት ነው።

ITA KEEPING SPORT REAL

አለምአቀፍ የምርመራ ኤጀንሲ -የአለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ በጨዋታዎች ወቅት ለሙከራ ሀላፊነት ለሚወስደው አለምአቀፍ የምርመራ ኤጀንሲ (አይ.ቲ.ኤ)የፀረ-ዶፒንግ ሀላፊነቶችን ሰጥቷል።

AIU

ኤ.አይ. ዩ-የአትሌቲክስ ኢንቲግሪቲ ዩኒት በፓሪስ ውስጥ ይገኛል ። እናም ከኢንተርናሽናል ኦሊምፒክ ኮሚቴ ወይም ለአለምአቀፍ ፈተና ኤጄንሲ ጋር በመተባበር በአትሌቲክስ ስፖርት ውስጥ ህጎችን በትክክል መተርጎሙን ያረጋግጣል።


# አስፈላጊ ቀናት

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 18 እስከ ጁላይ 17፣2024 የሚያካተት የቅድመ ጨዋታ ጊዜ በዚህ ጊዜ ዉስጥ የአትሌቲክሰ ኢንተግሪቲ ዩኒት አለም አቀፍ የምርመራ ኤጀንሲ እና ብሄራዊ የፀረ- አበረታች ቅመሞች (NADOs) አትሌቶችን ሊመረምሩ ይችላሉ።

እ.ኤ.አ ጁላይ 18፣2024 የኦሊምፒክ መንደሩ ይከፈታል፡፡ በውድድሩ ወቅት ምርመራው የሚከናወነው በአለም አቀፍ የምርመራ ኤጀንሲ ብቻ ነዉ፡፡ የአትሌቲክስ ኢንተግሪቲ ዩኒት አሁንም ከዝግጅቱ ስፍራዎች ውጭ ምርመራዎችን ሙከራዎችን ሊያደርግ ይችላል፡፡

እ.ኤ.አ ከኦገስት 01 እስከ ኦገስት 11 2024 በኦሊምፒክ ጨዋታዎች ወቅት የአትሌትክስ ውድድሮች ቀን ነው።

እ.ኤ.አ ኦገስት11 2024 የኦሊምፒክ ጨዋታዎች ፍጻሜ ነዉ።የአትሌትክስ ኢንተግሪቲ ዩኒቲ ከኦገስት 12 ጀምሮ ወደ ቀድሞ ስልጣኑ ይመለሳል።



# ምርመራ

## በውድድር ውስጥ እና ከውድድር ውጭ ጊዜ

ምንም እንኳን በውድድር ወቅት የማይወሰዱ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ከውድድር ውጪ ቢወሰድም በውድድር ጊዜ በሚደረግ ምርመራ ላይ በናሙና ውስጥ ሊገኝ ይችላል። ይህም ሊያስቀጣ ይችላል፣ ከውድድር ውጪ እንዲወሰዱ የተፈቀዱ እና በውድድር ውስጥ የተከለከሉ ንጥረነገሮች ከሰውነት ውስጥ የሚወጡበትን ሰዓት (washout period) መቼ እንደሚሆን ሀኪሞትን ያማክሩ። ከሰውነት ውስጥ የሚወጡበትን ሰዓት (washout period) ማለት የውድድር ጊዜ ከመጀመሩ በፊት የመጨረሻ የተሰጠበትን ሰዓት ማስላትን ይመለከታል።

በኦሊምፒክ ጨዋታዎች ወቅት የአይ.ኦ.ሲ የፀረ-አበረታች ቅመም ህጎች በውድድር ጊዜ ለተለያዩ የዶፒንግ ፍቺዎች እንደሚከተለው እንደሚተገበሩ ልብ ይበሉ።👇

| የውድድር ጊዜ | ከውድድር ጊዜ ውጪ |
|---|---|
| አትሌቱ እስከ ውድድር ፍፃሜው ድረስ ለመሳተፍ የታቀደበት ውድድር ከመጀመሩ ቀን በፊት 23:59ላይ የሚጀምር ሲሆን  አትሌቱ ውድድሩ እንኪያልቅ ድረስ ይወዳደራል።<br>"ውድድር" የሚለው ቃል በአይኦሲ ህግ ሲገለፅ "የአንድ ጊዜ ውድድር፣ግጥሚያ፣ጨዋታ ወይም የነጠላ ስፖርት ውድድር "<br>ለምሳሌ በአትሌቲክስ የ100ሜ.<br>ውድድር ፍፃሜ | ማንኛውም ከውድድር ጊዜ ውጪ የሆነ ጊዜ። ይህ ማለት በሁሉም ጊዜያት ማለት ነው። |

ምሳሌ፡-በነሐሴ 4፣የ1500ሜየግማሽ ፍፃሜ ውድድርን ለማካሄድ ቀጠሮ ተይዞለታል። እና የፍፃሜ ውድድር ደግሞ በነሐሴ 7 ይካሄዳል።ለግማሽ ፍፃሜው ውድድር የውድድር ጊዜ የሚሆነው ነሀሴ 3 ከ23:59 ሰዓት እስከ ነሀሴ 4 የግማሽ ፈፃሜ ውድድሩ አብቅቶ ምርመራው ባለቀበት ሰዓት ላይ ይሆናል።የፍፃሜ የውድድር ደግሞ ጊዜ ነሀሴ 6 ከ23:59 ሰዓት እስከ ነሀሴ 7 የፈፃሜ ውድድሩ አብቅቶ ምርመራው ባለቀበት ሰዓት ላይ ይሆናል።በነሀሴ 5 ባሉት ዙሮች መካከል ምርመራ ቢኖር  ይህ ምርመራ ከውድድር ውጪ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል።

# Therapeutic Use Exception (TUE)

lበህመም ምክኒያት የሚፈቀድ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች ለመውሰድ ፈቃድ ማግኘት (TUE)ስምዎ ለኦሊምፒክ ጨዋታዎች የመጨረሻ ተሰላፊ ዝርዝር ውስጥ ከሆነ እና የኦሎምፒክ መንደር ከመከፈቱ በፊት(እስከ ጁላይ 17 ጨምሮ) በአለም አትሌቲክስ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ህግ መሰረት (World Athletics Anti-Doping Rules) በህመም ምክኒያት የሚፈቀድ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች ለመውሰድ ፈቃድ ማግኘት (TUE) ፈቃድ ከኤአዩ ማግኘት የሚያስፈልግዎ ከሆነ ፡ምስጥረነቱ በሚጠበቅ ኢሜል tue@athleticsintegrity.orgኦሊምፒክ ጨዋታው ሊጀመሩ 30 ቀናት ሲቀረው በፊት(ድንገተኛ ወይም በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር) ለTUE ለ AIU ማመልከት ያስፈልግዎታል።ቀደም ሲል የነበሩት ፈቃድ መጠየቅያዎች የ አይኦሲ (IOC) እውቅና ያላቸው በመሆኑ የእርስዎን የፈቃድ ጥያቄ ለአይኦሲ  እንደገና ማስገባት አያስፈልግም።

የኦሎምፒክ መንደር ከተከፈተ በኃላ (ከጁላይ 18 ቀን 2024  ጀምሮ) TUE ከፈለጉ በፖሊ ክሊኒክ ዉስጥ ያለውን የአለምአቀፍ ምርመራ ኤጀንሲ( ITA) ቢሮ ማመልከት አለቦት። ሙሉ ሂደቱ እዚህ ድኅረ ገፅ ላይ ማግኘት ይቻላል ። https://ita.sport/tue-paris-2024/

ያስታወሱ ፡በአለም አቀፍ ኦሊምፒክ ኮሚቴ(IOC)  የተሰጡ የTUEs ፈቃዶች የሚሰሩት ለኦሊምፒክ ጨዋታዎች ጊዜ ብቻ ነዉ የምሰራዉ።

*ጭማሪ ማሻሽያ የተደረገባቸው የተከለከለ ዝርዝር*

የ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ጨዋታዎች የተከለከለ ዝርዝር ለፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ ጨዋታዎች ጥቅም ላይ ይውላል።በዝርዝሩ ውስጥ የተከለከሉትንና ከውድድር ውጪ የሆኑትን ሁሉንም ንጥረነገሮችና ዘዴዎች አካቶአል።
ማስታወሻ፡ትራማዶል፣ናርኮቲክ በጥር 01 2024 በውድድር  ጊዜ ላይ እንደየተከለከለ ንጥረ ነገር ተካቶአል።

# የመገኛ አድራሻ

በአትሌቶች የቀረበ መረጃ የምርመራ ባለስልጣኖች አትሌቶችን ከውድድር ውጭ ያለ ምንም ቅድመ ማሳወቅ በሞሉት አድራሻ መሰረት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። እስከ ኦሊምፒክ ጨዋታው ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ለዝግጅቶች፣ለማጣርያዎች ፣የሥልጠና ካምፖች በብዛት የሚጓዙ ከሆነ እባክዎን ወቅቱን የጠበቀና ትክክለኛ የመገኛ አድራሻ መሞላቱን ያረጋግጡ።

<table>
<tr><th></th><th>በምርመራ ቋት ውስጥ ላሉ<br>እና በክትትል ስር የተመዘገበ አትሌት</th><th>ሌሎች የዓለም አቀፍ<br>ደረጃ ለሚገኙ አትሌቶች</th></tr>
<tr><td>ወደ ኦሊምፒክ ጨዋታዎች መንደር ከመድረሱ በፊት</td><td>በፀረ ዶፒንግ ውጤት አስተዳደር እና ሥርዓት( ADAMS,) ፣በአትሌት ማዕከላዊ መተግበርያ ያሉበትን ክፍል ጨምሮ በዝርዝር የመገኛ አድራሻ መረጃ መሙላቱን መቀጠል ይኖርበታል።</td><td>የመገኛ አድራሻ መሙላት አይጠበቅባቸውም ።</td></tr>
<tr><td rowspan="2">በኦሊምፒክ ጨዋታ መንደር ውስጥ</td><td>በፀረ ዶፒንግ ውጤት አስተዳደር እና ሥርዓት( ADAMS,) ፣በአትሌት ማዕከላዊ መተግበርያ ያሉበትን ክፍል ጨምሮ በዝርዝር የመገኛ አድራሻ መረጃ መሙላቱን መቀጠል ይኖርበታል።</td><td>የመገኛ አድራሻ መሙላት አይጠበቅባቸውም ።</td></tr>
<tr><td colspan="2">ለኦሊምፒክ ጨዋታው ጊዜ የብሔራዊ ኦሊምፒክ ኮምቴዎ የክፍል መረጃዎን ለአለም አቀፍ ምርመራ ኤጀንሲ (ITA) ፣በ ITA Rooming App መተግበርያ አማካኝነት እንዲያሳውቅ ይጠበቅበታል። በጨዋታው ጊዜ ክፍሎችን ከቀየሩ በፀረ ዶፒንግ ውጤት አስተዳደር እና ሥርዓት(ADAMS,) ላይ በመሙላት ለብሔራዊ ኦሊምፒክ ኮምቴዎ ማሳወቅ አለብዎት።ይህን ማድረግ ካልቻሉ ህግ በመጣስ ሊጠየቁ ይችላሉ።</td></tr>
<tr><td>ከጨዋታዎች በኃላ</td><td>በፀረ ዶፒንግ ውጤት አስተዳደር እና ሥርዓት( ADAMS,) ፣በአትሌት ማዕከላዊ መተግበርያ ያሉበትን ክፍል ጨምሮ በዝርዝር የመገኛ አድራሻ መረጃ መሙላቱን መቀጠል ይኖርበታል።</td><td>የመገኛ አድራሻ መሙላት አይጠበቅባቸውም ።</td></tr>
</table>

በክትትል ስር*የተመዘገበ አትሌት ማለት በቅርቡ በምርመራ ቋት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ አትሌቶች ሲሆኑ ለአትሌትክስ ኢንተግሪት ዩኒት የተወሰነ መልኩ የመገኛ አድራሻዎቻቸውን ማሳወቅ አለባቸው፡

# የጫማ ህግጋትና ደንቦች



የአለም አትሌትክስ የአትሌትክስ ጫማ ህጎች World Athletics Athletic Shoe Regulations፣ በኦሎምፒክ ጨዋታዎች ላይ የትኞቹን ጫማዎች መልበስ እንደምትችሉ ይደነግጋል።

👟 የተፈቀደውን የጫማ ዝርዝሮች ይመልከቱ
የተፈቀደውን የጫማ ዝረዝሮችን ይመልከቱ በኦሊምፒክ ጨዋታዎች ወቅት በአለም አትሌትክስ የተፈቀደውን የጫማ ሞደሎችን ሊለብሱ ይችላሉ።እራሶዎን አስቀድመው በሚለብሱት ጫማ ስም እና ሞዴል እራስዎን በደንብ ማወቅ አለብዎት።
የተፈቀደዉን የጫማ ዝርዝር ለማየት ይጫኑ here.

እባካችው በእድገት እና በትዕዛዝ የተሰሩ ጫማዎች በኦሊምፒክ ጨዋታዎች ላይ ማድረግ አይፈቀድላቸዉም።

🦶ከጤና ጋር የተገናኙ የጫማ ማስተካከያዎች በተመለከተ፣ጫማዎን ለህክምና ምክንያቶች መቀየር ካለብዎት፣ለምሳሌ የጫማ ምቾት ማገዣ ማስተካከያ መሳርያዎች ለመጠቀም በቅድምያ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

ከኦሎምፒክ ጫዋታዎች ከመጀመሩ በፊት የአለም አትሌትክስ የሚወዳደሩበትን የጫማ አይነት እንዲያሳውቁ ሊጠየቁ ይችላሉ፣ ይሄም
1.የሚለብሱትን የጫማ ሞዴል እና 2.ይህ ጫማ እንዲደረጉ ከተፈቀደላቸው የጫማ ዝርዝር ውስጥ መካተቱን ለማረጋገጥ ነው።

✅ ከውድድር በኃላ የጫማ ቁጥጥር ፍተሻ ሊደረግ ይችላል፣ ይህም ውድድሩን ከጨረሱ በኃላ ሁልጊዜ የአትሌትክስ ጫማዎን ከእርሶ ጋር ይያዙ

ስለ አትሌትክስ ጫማ ደንቦች በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች በዚህ ድህረ-ገፅ in this document ላይ ይገኛሉ።

# ውድድር ማጨበርበር

ማንኛውም አይነት የውድድር ማጨበርበርን ለመከላከል በኦሎምፒክ ጨዋታዎች ላይ ጥብቅ ህጎች አሉ።

የውድድር ማጭበርበርን ለመከላከል በኦሎምፒክ የንቅናቄ ኮድ ስር እነዚህን ተግባራት ማድረግ አለባችሁ።

## በመጀመርያ አጋጣሚ የሚያውቁት ነገር ካለ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ

## ለሚደረጉ ማንኛውም አይነት ምርመራዎች መተባበር

ከጨዋታዎች ጋር በተያያዙ ዝግጅቶች ወይም ውድድሮች ላይ ( ከአትሌትክስ በስተቀር ስፖርቶችን ጨምሮ) ውርርድ አለማድረግ ወይም ውርርድ እንዲደረግ ማገፋፋት ወይም ማስተዋወቅ አይቻለም።

ከውድድር መጠቀምያ ወይም ሌላ ማንኛውንም አይነት ሙስና ጋር የተያያዙ ጥቅማ ጥቅሞችን አለመስጠት አለመፈለግ ወይም አለመቀበል።

ከጨዋታዎች ጋር በተያያዙ ዝግጅቶች ወይም ውድድሮች (ከአትሊትክስ ውጪ ባሉ ስፖርቶች ላይ ጨምሮ) ጥቅም ለማግኘት ሁን ተብሎ የውድድር ውጤቶችን መቀየር፡

የውስጥ መረጃን አለማካፈል



# ጥበቃ

የአለም አቀፉ ኦሎምፒክ ኮምቴ አትሌቶችን እና ሌሎች ተሳታፊዎችን ለመጠበቅ እና በጫወታዎቹ ወቅት ከሚደርስባቸው አላስፈላጊ እንግልትና ትንኮሳ ለማዳን ተተግብሮዋል፡፡
ይህ ማዕቀፍ በአትሌቲክስ ስፖርት የሚሳተፉ እውቅና ላላቸው ሁሉም ተሳታፊዎች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ድጋፍ በአለም አትሌቲክስ የድህነት ጥበቃ የማድረግ ህጉን የሚያግዝ ነው፡፡

በኦሊምፒክ ጨዋታዉ ላይ የአለም አትሌትክስ የድህነት ጥበቃ (Safeguarding) ኦፊሰር ያሎዎትን ማንኛውንም የድህነት ጥበቃ (Safeguarding) ስጋቶችን ለማዳመጥ ዝግጁ ነው፡፡ ይህም ከአለም አቀፍ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ጥበቃ ቡድን(Safeguarding Team )ጋር አብሮ ይሰራል፡፡ ከብሔራዊ ኦሊምፒክ ኮሚቴ የበጎ አድራጎት ኦፊስሮች ጋር በመተባበር ተገቢው እርምጃ በሚመለከተው አለም አቀፍ ኦሊምፒክ ስር መወሰዱን ያረጋግጣል፡፡

## በጨዋታዎች ጊዜ የማሳወቅያ መስመሮች(ሪፖርት) የሚከተሉት ናቸዉ።

·የአለም አቀፍ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ጥበቃ ኦፊሰር ወይንም ኦፊሰሮች እና ወይም በአለም አቀፍ የኦሊምፒክ መንደር ወይንም መንደሮች ለተሰየመው ልኡካን

የደህንነት ጥበቃ መኮንን ኢሜይል አድራሻ
safeguardingofficer@olympic.org

የተመደበው የደህንነት ጥበቃ አትሌቲክስ ጥበቃ ኦፊሰር:
safeguarding@worldathletics.org

የአለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ታማኝነትና ተገዢነትን በተመለከተ ጉዳይ የተዘረጋ የስልክ መስመር IOC Integrity and Compliance Hotline.

በአለም አቀፍ የኦሎምፒክ ኮምቴ ሰራተኞች በኦሎምፒክ መንደር ውስጥ በተዘጋጁ ደህንነቱ የተጠበቀ ስፖርት እንዲኖር በትጋት ይሰራሉ

የአትሌቱ 365 ድህረ ገጽ ደህንነቱ የተጠበቀ ስፖርት እንዲኖር የሚመለከተውን ክፍል ለማግኘት Safe Sport - Athlete365 (olympics.com).

በጨዋታዎች መንደር ውስጥ ከአካል ብቃት ማእከል በላይ በሚገኘው ደህንነቱ በተጠበቀ የስፖርት ዞን ሚስጥራዊ ድጋፍ እና ምክክር ይደረጋል፡፡

## በማሳወቅ (ሪፖርት) በማድረግ የበኩላችሁን ድርሻ ይወጡ

ከጨዋታዎች በፊት በማንኛዉም ጊዜ ወይም በኋላ ማንነታችሁ ሳይታወቅ ለአትሌትክስ ኢንተግሪት ክፍል ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ፡፡ የ QR ኮድ ይ
ይደውሉ ወይም በኢሜል ይላኩልን፡፡
+33 1 87 16 96 42
Confidentialreport@athleticsintegrity.org
www.athleticsintegrity.org/make-a-report

# ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎችና ሌሎች ሰነዶች፡

IOC Code of Ethics (including the Olympic Movement Code on the Prevention of the Manipulation of Competitions at page 83 and following): IOC Code of Ethics - Olympic Principles and Rules of Conduct (olympics.com)

IOC Anti-Doping Rules: https://olympics.com/ioc/fight-against-doping/medical-and-anti-doping-rules-for-the-games

የአትሌቶችን እና ሌሎች ተሳታፊ አካላት ደህንነትና ጥበቃን የሚመለከት የአይኦሲ ማዕቀፍ ፡IOC-Games-Time-framework-ENG.pdf (olympics.com)